# Grade 6 sciencebgh

## ሆርሞን

**የርዕሱ አላማ**

- የሆርሞኖችን ምንነት ትገልጻላችሁ
- አድሬናሊን ኢንሱሊን የተባሉትን ሆርሞኖች ተግባራት ታብራራላችሁ

**ስርዓተ ዝግ እጢ**

- ስርዓተ ዝግ እጢ የሰውነታችንን ተግባራት የሚቆጣጠርና የሚያስተባብር ስርዓት ሲሆን ቱቦ ወይም ቦይ የላቸውም
- ስርዓተ ዝግ ሆርሞኖች የሚባሉት ኬሚካል ውህዶች ያመነጫሉ፡፡

## ሆርሞኖች

- ሆርሞኖች የሰውነት ተግባራትን ይቆጣጠራል፡ ያስተባብራል በደም ተሸካሚነት መልዕክታቸውን ወደ ተፈላጊው የሰውነት ክፍል ያደርሳሉ፡፡

**ለምሳሌ፡-** የዕድገት ሆርሞኖች፤ ኢንሱሊን፤ አድሬናሊን እና ታይሮክሲን የሚባሉ ሆርሞኖች በሰውነታችን ውስጥ ይዘጋጃሉ፡፡

## አመንጪ ዕጢዎች እና ሆርሞኖች ተግባራት

1. **ታይሮይድ ዕጢ**፡- የሚባለው በአንገት አካባቢ የሚያመነጨው ሆርሞን ታይሮክሲን ባንድነትና ዕድገትን ይቆጣጠራል እጥረት የአእምሮ ዝግመትና የግንባንድት መፍጠን ያስከትላል፡፡
2. **ፒቱታሪ ዕጢ፡-** ከአንጎል ስር የሚገኝ ዕጢ ነው የዕድገት ሆርሞንን ያመነጫል የአጥንትና የጡንቻ ዕድገትን ይቆጣጠራል እጥረት ሲኖር ድንክነት እና የአእምሮ ዝግመት ሲያስከትል በብዛት ሲኖር ደግሞ ግዙፉነትን ያስከትላል፡፡

**መረጭ**፡- ከጨጓራ በስተጀርባ የሚገኝ ዕጢ ነው ሁለት አይነት ሆርሞኖች ያመነጫል

1) ኢንሱሊንና 2) ግሉካጎን ናቸው፡፡

- ሁለቱንም ሆርሞኖች በደም ውስጥ ያለው የስኳር መጠን ይቆጣጠራል፡፡

1. **ኢንሱሊን**፡- በመረጭ (pancrease) ይመነጫል የሰውነት ህዋሳቶቻችን ግሉኮስን እንዲጠቀሙ ያደርጋል ከመጠን በላይ የሆነ ግሉኮስ በደም ውስጥ ሲኖር ወደ ግላኮጂን በመቀየር ጉበት ውስጥ ያጠራቅማል፡፡
2. **ግሉካጎን፡-** ደም ውስጥ ያለውን የግሉኮስ መጠን ከሚያስፈልገው በታች ሲሆን ጉበት ውስጥ የተጠራቀመውን ግላይኮጂን ወደ ግሉኮስ በመቀየር በደም ውስጥ ግሉኮስ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

- የኢንሱሊን እጥረት በደም ውስጥ ሲኖር የስኳር በሽታ ይከሰታል ይህ ማለት ግሉኮስ ከሽንት ጋር ከሰውነት ይወገዳል ማለት ነው፡፡

## አድሬናሊን

- አድሬናሊን ዕጢዎች ከሁለት ኩላሊቶቻችን ላይ የተጠበቁ ሲሆኑ የሚያመነጩትም ሆርሞን አድሬናሊን በመባል ይታወቃል አድሬናሊን ፍርሀትን፤ ቅጽበት፤ ድንጋጤና ቁጣ ሲኖር በከፍተኛ ሁኔታ በመመንጭ ለሰውነታችን ሀይል ይሰጠናል፡፡ (ገጽ185)

# <u>አደንዛዥ እጽ እና ሱስ አምጪ መድሀኒቶች</u>

<u>የርዕሱ ዓላማ</u>

- በተፈጥሮ ወይም የተቀመሙ ሱስ አምጪ መድሀኒቶች መሆናቸውን ትጠቅሳላችሁ
- አደንዛዥ ዕጾች በግለሰቦችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሊስከትሉ የሚችሉ ጎጂ ውጤቶች ታብራራላችሁ፡

- በሀገራችን የሚገኙ ሱስ አምጪ እጾችና ኬሚካሎች ትምባሆ አልኮል፤ ጫትና ሀሺሽ ናቸው እነዚህ እጾች በተደጋጋሚ ሲወሰዱ ወደ ሱስነት የመቀየር ባህሪን የመቀየርንና ተጠቃሚውን በተጽዕኖ ስር ከማድረግ ሌላ ሞትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በተጨማሪም የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ ተጽንኦዎች ያስከትላሉ፡፡

**<u>አልኮል፡-</u>** በውስጡ ኢታኖል የተባለ ውህድ የያዙ ሲሆን የነርቭ **<u>ኢታኖል</u>** የማዕከላዊ ስርዓተ ነርቭ ያደነዝዛል ህዋሳትን ይገድላል የማሰብ ችሎታን ይቀንሳል፤ ያኮላትፋል ያንገዳግዳል በተጨማሪ ግንፍል ግንፍል ያሰኛል፡፡

## <u>ሲጋራ</u>

<u>ሲጋራ</u>፡- በውስጡ ኒኮቲን የተባለ ከትምባሆ ቅጠል የሚገኝ ቅመም የያዘ ነው፡፡

**<u>ኒኮቲን፡-</u>** አንጎል ያነቃቃል፤ የልብ ምትን ያፋጥናል የደም ግፊት ይጨምራል፤ ለካንሰር በሽታና ለሳንባ በሽታ ያጋልጣል፡፡

## <u>ጫት</u>

**<u>ጫት</u>፡-** በውስጡ ካቴኒን የተባለ ውህድ ይዟል ጫትን የሚጠቀሙ ሰዎች

- ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ይደርስባቸዋል
- የሆድ ድርቀት፤ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፤ መቅበጥበጥ የጥርስ መበላሸትና የአዕምሮ ችግር የቅን ህልም ያጋጥማቸዋል፡፡

## <u>የተቀናጀ ሳይንስ ተሳትፎ ጥያቄዎች ሁለት</u>

## <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ</u>

1. ከትምባሆ ቅጠል የሚዘጋጀው ሲጋራ በውስጡ ምን የተባለ ቅመም ይይዛል ?
2. በሀኪም ትዕዛዝ ብቻ ለህመም ማስታገሻነት የሚሰጡ መድሀኒቶች እነማን ናቸው ?
3. የኢንሱሊን መድሀኒቶች እነማን ናቸው ?
4. በሁለቱ ኩላሊቶቻችን ላይ የሚገኙ ዕጢዎች እነማን ናቸው ?
5. የአልኮል በሰውነታችን ላይ የሚያደርሰውን ተጽእኖ ዘርዝሩ ?
6. ታይሮይድ ዕጢዎች በየትኛው ሰውነት ክፍላችን ላይ ይገኛሉ ?

በ"ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ዕጢዎች "ለ" ስር ከተዘረዘሩት ሆርሞኖች ጋር አዛምዱ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ___________ **7** መረጭ | ሀ. አድሬናሊን |
| ____________ 8 ታይሮይድ | ለ የእድገት ሆርሞን |
| ____________ 9 አድሬናል | ሐ. ቅጽበት |
| ____________ 10 ፒታሪ | መ. ግሉካጎን |
| | ሠ. ታይሮክሲን |

## የተቀናጀ ሳይንስ ወርክሽት ሁለት

## የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ

1. ቱቦ ወይም ቦይ የሌላቸው እጢዎች ማን ይባላሉ ?
2. የሆርሞኖችን ተግባራት ዘርዝሩ ?
3. መረጭ (pancrease) የሚያመነጫቸውን ሁለት የሆርሞን አይነቶች ጻፉ ?
4. የስኳር (ግሉኮስ) መጠንን የሚቆጣጠሩ ሆርሞኖችን እነማን ናቸው ?
5. አልኮል ውስጥ የሚገኝ ውህድ ማን ይበላል ?
6. ጫት ውስጥ የሚገኝ ውህድ ማን ይበላል ?
7. ስንፈራ፤ ስንደነግጥ እና ስንቆጣ በከፍተኛ ሁኔታ የሚመነጭ ሆርሞን ማን ይባላል ?
8. የኢንሱሊን እጥረት በደማችን ውስጥ ሲኖር የሚከሰተው የበሽታ አይነት ማነው የሚገኝ ውህድ ማን ይበላል ?
9. የግሉኮስ መጠን በደማችን ውስጥ ከሚያስፈልገው በታች ሲሆን ግላይኮጂንን ወደ ግሉኮስ በመቀየር ወደ ደም ውስጥ የሚያስገባው ሆርሞን----------------------ይባላል፡፡
10. በሀገራችን የሚገኙ ሱስ አምጪ እጾችና ኬሚካሎችን ዘርዝሩ የሚገኝ ውህድ ማን ይበላል ?